የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፭
አዲስ አበባ — ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 15
ADDIS ABABA – 26th December 1996


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................................ ገጽ ፫፻፲፭


## CONTENTS


Proclamation No. 58/1996
Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation ........................................ Page 315


## አዋጅ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፹፱

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ የኢኮኖሚ ልማት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፯ ሚሊዮን ፮፻ ሺህ ኩ.ዲ (ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ የኩዌት ዲናር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ ኢኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኤፕሪል ፬ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከኩዌት ፈንድ ለአረብ የኤኮኖሚ ልማት ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 58/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE KUWAIT FUND FOR ARAB ECONOMIC DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development stipulating that the Kuwait Fund for Arab Economic Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 7,600,000 K.D. (seven million and six hundred thousand Kuwaiti Dinars) for partly Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project, was signed in Addis Ababa, on the 4th day of April, 1996;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 26th day of December, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Kuwait Fund for Arab Economic Development Loan Agreement for Financing the Addis Ababa Bole International Airport Development Project Ratification Proclamation No. 58/1996."

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኩዌት ፈንድ ለአረብ የኤኮኖሚ ልማት መካከል እ.ኤ.አ. ኤፕሪል ፬ ቀን ፲፱፻፺፮ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር ፬፻፺፬ የብድር ስምምነት ነው ።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፯ ሚሊዮን ፮፻ሺህ ኩ.ዲ. (ሰባት ሚሊዮን ስድስት መቶ ሺህ የኩዌት ዲናር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 494 signed in Addis Ababa, on the 4th day of April 1996 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Kuwait Fund for Arab Economic Development.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 7,600,000 K.D (seven million and six hundred thousand Kuwaiti Dinars) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 26th day of December, 1996.

Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE